**Concerned Ethiopians in Toronto Coordinating Committee**

998 Bloor St. W., P.O. Box 10666, Toronto M6H 1L8

## አገር እና ታሪክ የማዳን ተግባርና ሃላፊነት የሁሉም ዜጋ ግዴታ ነው

አገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት የውስጥና የውጭ ጠላቶችና ብዙ ፈተናዎች ቢገጥሟትም፣ በፈጣሪዋ ሀይልና በህዝቡ ከፍተኛ መስዋዕትነት የገጠሟትን ፈተናዎችና ችግሮች ተቋቁማ አኩሪ ታሪክዋን ጠብቃ፣ የቀድሞው አባቶቻችን ይህችን አገር አስረክበውን አልፈዋል። በታሪኩዋ ግን እንደ አሁን አይነት ከፍተኛ አደጋ፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የማጥፋት ስራ የሚሰራ ጠላት ለዚያውም የውስጥ ጠላት አጋጥሟት አያውቅም።

ሕዝብን በቋንቋና በዘር ከፋፍሎ አንድ የነበረውን ህዝብ በማለያየት፣ የገሪቷን ታሪክና ጥንታዊ ቅርሷን እያጠፋና እየደመሰሰ አዲስ የሀሰትና የፈጠራ ታሪክ እየፈጠረላት መጪውን ጊዜ እያጨለመ ወጣቱ ትውልድ የሚረከባት አገር እያሳጣን ነው።

ወያኔ ጥቃት ከከፈተባቸው ተቋማት መካከል አንደኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እና ገዳማት ላይ ነው። ቅዱስ ፓትርያርኩ በህይወት እያሉ በላያቸው ላይ ሌላ ፓትርያርክ አባ ጳውሎስን ከሾመ ጊዜ አንስቶ በአንድነቷ ጸንታ የቆየችው ቤተክርስቲያን ተከፍላ ከሃያ አመት በላይ ችግሩ መፍትሔ ሳያገኝ አባቶችና ምዕመናን እንዳዘኑ ኖረዋል።

በተደጋጋሚ በአብያተ ቤተክርስቲያን እና ገዳሞች በእሳት እየጋዩ ተጠብቀውና ተከብረው የነበሩ የእምነትና የታሪክ ስፍራዎች ሆን ተብሎ እንዲጠፉ እየተደረገ ነው። በቅርቡ በዝቋላ አቦ ገዳም ላይ ለጥፋት የተለኮሰው እሳት ከፍተኛ ውድመት አድርሷል። በዋልዳባ ገዳም ከሺህ አመታት በላይ የእምነት የታሪክ ቦታ የሆነውን ገዳም ለአንድ ከበርቴ የንግድ ቦታ ለማድረግ በማሰብ በእሳት ጋይቷል።

የህጋዊ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቅዱስ ሲኖዶስ በወቅቱ የጥፋት ድርጊቱን በማውገዝ መግለጫ አውጥቷል። ቅዱስ ሲኖዶስ በየጊዜው መንፈቃዊ ወይም አመታዊ ስብሰባ ባደረገ ቁጥር የወያኔን ጥፋትና የህዝብ ሰቆቃ በማውገዝና በመኮነን መግለጫዎችን ያላወጣበት ጊዜ የለም። አባቶች ታሪካዊ ሃላፊነታቸውን በመወጣት፣ በማዘንና በጸሎት በመትጋት የሚችሉትን ሁሉ በማድረጋቸው ትልቅ መጽናናትን አግኝተናል።

በዋልድባና በሌሎችም ገዳማት ላይ የሚደርሰውን ጥፋት ለማውገዝ በቶሮንቶ የመንበረ ጽባኦት ቅድስት ማርያም ካቴድራል አባቶች ባስተላለፉት መልእክት ምእመናን ሁሉ በአንድ ላይ ወጥቶ ድርጊቱን እንዲያወግዝ፣ በጸሎትና በለቅሶ ፈጣሪን እንዲለምን ማሳሰባቸው፣ ሃላፊነታቸውን መወጣታቸው፣ የሚደገፍና የሚበረታታ ነው። ድጋፋችንን አብረን በመሰለፍ እናሳያለን፣ ሌሎችም እንዲወጡ እንቀሰቅሳለን።

የሀይማኖት አባቶች አገር ሲጠፋ፣ ታሪክ ሲወድም፣ ህዝብ ሲሰቃይ፣ ድርጊቱን ማውገዝና ድምጽን ማሰማት አለባቸውና ወደፊትም ህዝቡና በማስተባበር ለህዝብ፣ ለአገር፣ ለእውነት፣ ለታሪክ፣ ለፍትህ፣ ለሰላም በሚጮኹበት ቦታ ሁሉ አብረናቸው መጮህና መሰለፍ ይኖርብናል። እኛም የአገራችን ጉዳይ የሚያሳስበን የሚቆረቁረን ሁሉ ከጎናቸው የምንሰለፍ መሆኑን ለማሳወቅ እንወዳለን።

እግዚአብሔር አገራችንን ኢትዮጵያን ይጠብቅልን!

ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን በቶሮንቶ

ሚያዝያ 8 ቀን 2004 ዓ/ም